አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

# የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና አጠቃቀም ፈቃድ አሰጣጥ እና አፈጻጸም

## መመሪያ ቁጥር 156/2016

በከተማው ውስጥ የሚገኘውን የከርሰ ምድር ውሃ ሃብት ፍትሃዊና ዘላቂ በሆነ መንገድ በማልማት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማስቻል ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች የራሳቸውን አማራጭ የውሃ መገኛ እንዲያጎለብቱ እና እንዲጠቀሙ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በከተማው ውስጥ የራሳቸውን የውሃ ጉድጓድ አዘጋጅተው እየተጠቀሙ ያሉ እንዲሁም በራሳቸው ተነሳሽነት የጉድጓድ ቁፋሮ ፍቃድ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ሰዎች ፍቃድ መስጠት፣ ቁፋሮውን አጠናቀው ከጨረሱ በኋላ የአጠቃቀም ፍቃድ ለመስጠትና በቂ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ በማስፈለጉ፤

በከተማው ውስጥ የሚቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶች ደረጃቸውን የጠበቁና ውስን የከርሰ ምድር ሀብቱን መጠን በማይጎዳ መልኩ ሥራ ላይ ለማዋልና በቁፋሮና አጠቃቀም ጉድለት ምክንያት የሀብት ብክነት መቀነስ በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 16(2) (ሠ) እና 16(20) (መ)መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ መመሪያ “የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና አጠቃቀም ፈቃድ አሰጣጥና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 156/2016” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

   1. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
   2. **“ባለስልጣን”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ነው፤
   3. **“ዋና ሥራ አስኪያጅ”** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው፤
   4. **"አማራጭ የውሃ መገኛ"** ማለት ባለስልጣኑ ከሚያቀርበው ንጹህ ውሃ ውጪ ሌላ ማንኛውም የውሃ መገኛ ማለት ሲሆን የጉድጓድ ውሃ፣ የዝናብ ውሃ ፣ የወንዝ ውሃ ፣

የምንጭ ውሃ፣ ጥልቅ የከርሰምድር ውሃን፣ከፍሳሽ ውሃ የተጣራ ውሃ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ፤

5. **"የከርሰ ምድር ውሃ አጠቃቀም ፍቃድ"** ማለት ጠያቂው አካል ጉድጓዱን አስቆፍሮ ከጨረሰ በኋላ በሚደረግ በአቅም ፍተሻ ውጤት በተገኘው ውሃ መጠን መሰረት በሚወሰድ የውሃ ናሙና ጥራት ምርመራ ውጤት መነሻ ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ ውሃውን በቀን ውስጥ ለራሱ ፍጆታ የሚያስፈልገውን የውሃ መጠን ብቻ መጠቀም እንዲችል በባለስልጣኑ የሚሰጥ ፍቃድ ነው፤
6. **"የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፍቃድ"** ማለት በከተማው ክልል የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ለመቆፈር ለሚፈልግ ፍቃድ ጠያቂ በባለስልጣኑ የሚሰጥ ፍቃድ ነው፤
7. **"የከርሰ ምድር ውሃ"** ማለት ከመሬት ገፅ በታች የሚገኝ ውሃ ነው፤
8. **"የተበከለ ውሃ"** ማለት ከፍሳሽና ከፋብሪካዎች የሚወጣ ቆሻሻ ውሃ ወይም መርዛማ ውሃ ነው፤
9. **"የውሃ ብክለት"** ማለት ተፈጥሯዊ ወይም ኢንኦርጋኒክ ይዘት ያላቸውን ነገሮች በመጠቀም እንዲሁም በውሃው የሙቀት መጠን ለውጥ ምክንያት የሚከሰት የውሃ ብክለት ነው፤
10. **"የውሃ ጥራት"** ማለት በፊዚካል፣ በኬሚካል፣ በማይክሮ ባዮሎጂካል ፣ በባክቴሪዮሎጂካል እና ራዲዮሎጂካል ገፅታው በሚታወቀው ወይም በሚገኘው ውጤት መሰረት የሚገኝ የውሃ ጥራት መግለጫ ነው፤
11. **"ከፍተኛ ውሃ ተጠቃሚ ደንበኛ"** ማለት የ12 ወር ንባብ ተወስዶ በአማካኝ በወር 100 ሜትር ኪዩብ እና ከዚያ በላይ ውሃ ተጠቃሚ ደንበኛ ነው፤
12. **"የውሃ ጥራት ደረጃዎች"** ማለት የአለም ጤና ድርጅት ባፀደቀው የውሃ ጥራት ደረጃዎች ጋይድ ላየን እና የኢትዮጵያ ደረጃ መዳቢ ኤጀንሲ በህግ በተሠጠው ስልጣን መሰረት ያወጣው አገር አቀፍ ስታንዳርዶች መሰረት ሊጠበቁ የሚያስፈልጉትንና የሚፈቀዱትን ደረጃዎች በመወሰን የሚደረግ መለኪያ እና የጥራት አወሳሰን ነው፤
13. **"የውሃ ሥራዎች"** ማለት የውሃ ሃብትን ጠቀሜታ ላለው ተግባር ለማዋል የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ማናቸውም ሰው ሰራሽ ሥራዎች ሲሆኑ ይህም መጥለፍን ፣ መገደብን ፣መቆፈርን ወይም መሰርሰርን፣መጥረግን፣ መመርመርን፣ መቆጣጠርን ፣ ማጣራትን፣መለካትን፣ ማጓጓዝን፣ ማስተላለፍን ፣ጨው አልባ ማድረግን፣ ጎርፍ መከላከያ መገንባትንና ሌሎች ተዛማጅና የመሳሰሉ ሥራዎችን ማከናወንን ያጠቃልላል፤

14. **"የውሃ ሃብት አስተዳደር"** ማለት የውሃ ሃብት አጠቃቀምን፣መንከባከብን፣ ከብክለት እና ከብክነት መጠበቅንና መቆጣጠርን የሚመለከቱት ግባራትን ያካተተ ነው፤
15. **"የውሃ ጉድጓድ"** ማለት በእጅ ከሚቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶች ውጪ ለተለያዩ አገልግሎቶች የተለያዩ መሳሪያዎችን ወይም ሪግ በመጠቀም የከርሰ ምድር ውሃ አመንጪ ወይም አስተላለፊ አካሎችን በመዝለቅ የሚቆፈር ጉድጓድ ነው፤
16. **"የጉድጓድ ውሃ አቅርቦት"** ማለት ለመጠጥ፣ ለከተማ ግብርና፣ ለኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች አገልግሎቶች የሚቆፈር ጉድጓድ ነው፤
17. **"የውሃ አጠቃቀም"** ማለት ውሃን ለመጠጥ፣ለከተማ ግብርና፣ለኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች አገልግሎቶች መጠቀም ነው፤
18. **"የከርሰ ምድር ውሃ አጠቃቀም ዕድሳት"** ማለት ጠያቂው አካል ገድጓድ አስቆፍሮ ከጨረሰ በኋላ በተገኘ የውሃ መጠን እና በተወሰደ የውሃ ናሙና ውጤት መነሻነት ለሚፈቀድ አገልግሎት የመጠቀሚያ ፈቃድ ተሰጥቶት መጠቀም እና አገልግሎት ማግኘት ከጀመረ በኋላ በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው ጊዜ በባለስልጣኑ በኩል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
19. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. **<u>የጾታ አገላለጽ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

4. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ፡-

1. በአስተዳደሩ ውስጥ በሚገኙ ለመጠጥ ወይም ለሌላ ማንኛውም አገልግሎት የሚሆን አማራጭ የከርሰ ምድር የውሃ ምንጭ ማጎልበት በሚፈልጉ ፤ አማራጭ የከርሰ ምድር ውሃ ምንጭን አጎልብተው በመጠቀም ላይ ባሉ ሰዎች ላይ እና በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፤
2. በአዲስ አበባ ከተማ ወስጥ የመዓድን ውሃ ለማምረት የሚጠየቅ ፍቃድ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የከረሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ወይም አጠቃቀም ፈቃድ አሰጣጥና መስፈርቶች</u>

5. **<u>ስለ ፈቃድ አስፈላጊነት</u>**

ማንም ሰው ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ የውሃ ሥራዎችን መገንባት፣ከገነባው የውሃ ሥራ ወይም ከቆፈረው የውሃ ጉድጓድ የሚገኘውን ውሃ መጠቀም፤ ሌላ ሰው እንዲጠቀመው ማድረግ ለሌላ ሶስተኛ ወገን በማንኛውም መንገድ ማስተላለፍ አይችልም፡፡

6. **የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች እና ሂደት በጠቅላላው**

1. ማንኛውም ሰው የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፈቃድ ለማግኘት፣ የከርሠምድር ውሃ የመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት ወይም የመጠቀሚያ ፈቃድን ለማደስ በቅድሚያ ለባለስልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፤
2. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት፣ የከርሠምድር ውሃ የመጠቀም ፈቃድ ለመስጠት፣ የመጠቀሚያ ፈቃድን ለማደስ የሚቀርብ ማመልከቻ እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን መረጃዎችን እንደአግባብነቱ መያዝ አለበት፡-

   ሀ) የአመልካቹን ስምና ቋሚ አድራሻ፤

   ለ) የውሃ ሃብቱ የሚገኝበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ልዩ ቦታ፤

   ሐ) የውሃ ሃብቱ ጥቅም ላይ እንዲውል የታቀደበት የአገልግሎት አይነት፤

   መ) በየወሩ እና በየዓመቱ ሊወሰድ የታቀደውን የውሃ መጠን፤

   ሠ) በምን አይነት ዘዴ ወይም ሁኔታ ውሃውን ወስዶ ለመጠቀም እንደታቀደ፤

   ረ) በየወሩ እና በየዓመቱ ጥቅም ላይ የዋለ የውሃ መጠን መረጃ ወይም በጉድጓድ አናት ላይ በተገጠመ የውሃ ቆጣሪ ጥቅም ላይ የዋለ የውሃ መጠን የቆጣሪ ንባብ፤

   ሰ) ጥቅም ላይ ሊውል የታሰበን ወይም ጥቅም እየሰጠ ያለ ጉድጓድ አናት ላይ ጥቅም ላይ የዋለ የውሃ መጠን ለመለካት የሚያስችል የተተከለ የውሃ ቆጣሪ መረጃ የቆጣሪው ስፋት እና መለያ ቁጥር፤

   ሸ) በአመልካቹ ስም የገባ የቀጥታ ውሃ መስመር አገልግሎት ማረጋገጫ ወቅታዊ የውሃ ቢል ኮፒ፤

   ቀ) ደረጃውን የጠበቀ የተሟላ የከርሰምድር ፖተንሻል ሀድሮጂኦሎጂ እና የቦታ መረጣ ጥናት፣

   በ) የጉድጓድ ቁፋሮ ፣ፓምፕ ቴሰት እና ትንተና በአማካሪው ድርጅት እና በባለቤቱ ማህተም የተረጋገጠ ሪፖርት ያካተተ፤

   ተ) የጉድጓድ አጠቃቀም ምርት በድርጅቱ ማህተም የተደገፍ አጭር ርፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፤

   ቸ) ባለስልጣኑ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸው ዝርዝር የከርሰ ምድር ጥናቶችና ተያያዥ መረጃዎች፡፡

7. **ስለግል ድርጅት**

በአንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የከርሰ ምድር የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና የአጠቃቀም ፈቃድ ጠያቂው አካል የግል ድርጅት ሲሆን የሚከተሉት ሊሟሉ ይገባል፡-

1. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ደብተር ዋናውና ፎቶ ኮፒውን፤
2. ባለ ይዞታው ወይም የድርጅቱ ባለቤት ወይም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፓርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒውን፣በመያዝ ባለይዞታው በአካል ሲቀርብ ብቻ አገልገሎቱን ለማግኘት ይቻላል፤
3. የድርጅቱ ባለቤት ወይም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በተለያየ ምክንያት የማይገኝ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ፣
   ሀ) ውል ለመዋዋል ወይም አገልግሎቱን ፈቃድ ለመጠየቅ የሚያስችል በባለይዞታው ወይም በድርጅቱ ባለቤት ወይም በድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የተሰጠ ሕጋዊ ውክልና ዋናውና ፎቶ ኮፒ፣
   ለ) የተወካይ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመንጃ ፍቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒ፤

   በመያዝ ተወካዩ በአካል ሲቀርብ ብቻ አገልገሎቱን ለማግኘት ይቻላል፡፡

8. <u>**ስለመንግስት ተቋም**</u>

በአንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የከርሰ ምድር የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና የአጠቃቀም ፈቃድ ጠያቂው አካል  የመንግስት ተቋም ከሆነ የሚከተሉት ሊሟሉ ይገባል፡-

1. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ደብተር ዋናውና ፎቶ ኮፒውን፤
2. ከተቋሙ ጉዳዩን የሚያስፈፅም ተወካይ ሕጋዊ ውክልና ዋናውና ፎቶ ኮፒ፣ የተወካይ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመንጃ ፍቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ተወካዩ በአካል ሲቀርብ ብቻ አገልገሎቱን ለማግኘት ይቻላል፡፡

9. <u>**የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን**</u>

በአንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት ጠያቂው አካል  የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን  ከሆነ የሚከተሉት ሊሟሉ ይገባል፡-

1. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ደብተር ዋናውና ፎቶ ኮፒውን፤
2. ከሚመለከተው የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጉዳዩን የሚያስፈፅም ተወካይ ሕጋዊ ውክልና ዋናውና ፎቶ ኮፒ፣ የተወካይ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመንጃ ፍቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ተወካዩ በአካል ሲቀርብ ብቻ አገልገሎቱን ለማግኘት ይቻላል፡፡

10. <u>**ጠየቂው አካል  የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ**</u>

በአንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት ጠያቂው የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ከሆነ የሚከተሉት ሊሟሉ ይገባል፡-

1. ይዞታውን ከሚያስተዳድረው ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ወይም ጽህፈት ቤት በይዞታው ላይ የጉድጓድ ቁፋሮ እንዲያከናውን የሚፈቅድ የትብብር ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፤
2. ከሚመለከተው የከተማው ወይም የክፍለ ከተማው የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ጉዳዩን የሚያስፈፅም ተወካይ፣ የተወካይ ሕጋዊ ውክልና ዋናውና ፎቶ ኮፒ፣ የተወካይ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመንጃ ፍቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ተወካዩ በአካል ሲቀርብ ብቻ አገልገሎቱን ለማግኘት ይቻላል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ጠያቂው አካል የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ወይም የአርሶ አደር እና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ከሆነም ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

11. <u>**ስለ የማህበር ይዞታ**</u>

በአንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የከርሰ ምድር የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና የአጠቃቀም አገልግሎት ጠያቂው አካል ማህበር ከሆነ የሚከተሉት ሊሟሉ ይገባል፡-

1. በማህበሩ ስም የተዘጋጀ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ደብተር ዋናውና ፎቶ ኮፒው፣
2. የማህበሩን ህጋዊነት የሚገልፅ ማህበሩ ሲመሠረት ለማህበሩ እውቅና ከሠጠው የመንግስት ተቋም በማህተም የተረጋገጠ ደብዳቤ እና የማህበሩን አባላት እና አመሠራረት የሚያሳዩ ተያያዥ ሠነዶች ዋና እና ፎቶ ኮፒ፤
3. የማህበሩ ሊቀመንበር ወይም ህጋዊ ወኪሉ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒውን፡፡

12. <u>**ስለ ሪል እስቴት**</u>

በአንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የከርሰ ምድር የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና የአጠቃቀም አገልግሎት ጠያቂው አካል ሪል እስቴት ከሆነ የሚከተሉት ሊሟሉ ይገባል፡-

1. በሪል እስቴቱ ስም የተዘጋጀ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ደብተር ዋናውና ፎቶ ኮፒውን፣
2. የሪል እስቴቱን ህጋዊ ፈቃድና እውቅና ፣ የሪል እስቴቱን የንግድ ፈቃድ ፣ የሪል እስቴቱን አመሠራረት የሚያሳዩ ተያያዥ ሠነዶች ዋና እና ፎቶ ኮፒ፤

3. የሪል እስቴቱ አልሚ ወይም ሥራ አስኪያጅ የሪል እስቴቱ አልሚ ወይም ሥራ አስኪያጅ መሆኑን የሚያስረዳ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ህጋዊ ማስረጃ ፣ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፓርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒ፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሪል እስቴቱ አልሚ ወይም ሥራ አስኪያጅ ህጋዊ ውክልና የተሠጠው ተወካይ ሕጋዊ ውክልና ዋናውና ፎቶ ኮፒ፣ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመንጃ ፍቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒ በመያዝ አገልገሎቱን ለማግኘት ይቻላል፡

13. <u>የከርሠምድር ጉድጓድ ውሃ ቁፋሮ ፈቃድ ማመልከቻዎችና አፈፃፀማቸው</u>

1. የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ሥራ ለመሥራት፣ለማደስ ወይም የመለወጥ ፈቃድን በተመለከተ የሚቀርብ ማመልከቻ ለባለስልጣኑ መቅረብ አለበት፤

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ሥራውን ዲዛይን፣ ደረጃውን የጠበቀ የተሟላ የከርሰምድር ፖተንሻል ሀድሮጂኦሎጂ እና የቦታ መረጣ ጥናት፣ የጉድጓድ ቁፋሮ ዲዛይን እና ሰፔስፊኬሽን፣ ፓምፕ ቴሰት ትንተና ዘዴን የያዘ አጭር ሪፖርት ያካተተ ሙሉ ዝርዝር ጥናት መሆን አለበት፤

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ሥራ ለመሥራት ፣ ለማደስ ወይም ለመለወጥ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ እንዳግባብነቱ የዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 እስከ 12 እና ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

14. <u>ስለቁፋሮ የጊዜ ሠሌዳ</u>

1. ባለስልጣኑ የፈቃድ ደብዳቤ ወጭ ካደረገበት ዕለት ጀምሮ ቁፋሮውን እንዲያጠናቅቅ በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ ሥራውን ማከናወኑን ለመከታተል ያስችል ዘንድ የቁፋሮ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የቁፋሮ ሥራውን የሚያሳይ ዝርዝር የጊዜ ሠሌዳ ለባለስልጣኑ በደብዳቤ ማሳወቅና ማቅረብ አለበት፤ፈቃድ ጠያቂው ይህን ሳያቀርብ የሚያከናውነው ማንኛውም የቁፋሮ ሥራ ተቀባይነት አይኖረውም፤

2. የከርሠምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፈቃድ ጠያቂ አካል በሚያቀርበው የቁፋሮ የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ቁፋሮውን ሲጀምር፣ ቁፋሮውን አጠናቆ ኬዚንግ ለማስገባት ሲዘጋጅ እና አጠናቆ የጉድጓድ ውሃውን መጠን ለማወቅ የፍተሻ ሥራ ሲያከናውን

የባለስልጣኑ ባለሙያዎች የመስክ ላይ ክትትል እንዲያደርጉ ለባለስልጣኑ በደብዳቤ ማሳወቅ ይገባዋል፤

3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለጸው ሳይሟላ የሚያከናውን የቁፋሮ ሥራ ተቀባይነት የለውም ሆኖም የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ፈቃድ ጠያቂ አካል የባለስልጣኑ ባለሙያዎች እንዲገኙ አሳውቆ ባለስልጣኑ በራሱ ችግር ባለሙያዎችን ወደ መሰክ ሳይልክ ቢቀር ፈቃድ ጠያቂው አካል ተጠያቂ አይሆንም፤

4. የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ፈቃድ ጠያቂ ያቀረበው የከርሠ ምድር ውሃ ቁፋሮ ፈቃድ ተቀባይነት አግኝቶ ፈቃድ ማግኘቱን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከባለስልጣኑ ከተሠጠው በኋላ በተለያዩ አስገዳጅ ምክንያቶች በባለስልጣኑ በአስገዳጅነት የተቀመጡ የአሠራር መመሪያዎችን ጠብቆ ለመሥራት ችግር ሲገጥመው የገጠመውን ችግር አስገዳጅነት የሚገልፅ የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ አሳውቆ ቀድሞ የተሠጠው ፈቃድ እንዲታደስለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

15. <u>ፈቃድ አሰጣጥ</u>

በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ 5 እስከ 11 የተደነገጉት እንደተጠበቅ ሆኖ የከርሰ ምድር ውሃ አጠቃቀም ፈቃድ የሚሰጠው ፡-

1. ለፈቃድ ጠያቂው የከርሰ ምድው ውሃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ቢሰጠው በውሃ ሃብቱ የመጠቀም ህጋዊ መብት ያለው እና በውሃ ሃብቱ ህጋዊ ፈቃድ በማግኘት እየተጠቀመ ባለ ሰው ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማያደርሰ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. ፈቃድ ጠያቂው በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች፣ ግዴታዎችና መመዘኛዎች ያሟላ እና የሚያሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
3. በውሃ ሃብቱና በአከባቢው ላይ ጎጂ ውጤትን ወይም ብክለትን የማያስከትል መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን ባለስልጣኑ መስፈርት ያሟላ ማመልከቻ ሲቀርብለት ማመልከቻው ከቀረበበት ግዜ ጀምሮ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ለጠያቂው ፈቃዱን ሊሰጠው ይገባል፡፡ ሆኖም በቂ እና ተሟላ መረጃ ካልቀረበለት ባለስልጣኑ ፈቃዱን ሊከለክል ይችላል፡፡ የከለከለበትን ምክንያት ለፈቃድ ጠያቂው በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
4. ፋቃድ የተከለከለው ፈቃድ ጠያቂ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡ ባለስልጣኑም ቅሬታውን ተቀብሎ በ10 ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ወሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

16. <u>ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበትና የሚራዘምበት ሁኔታ</u>

1. በባለስልጣኑ የሚሰጠው የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ በየጊዜው በሚኖር መሰል የፕሮጀክት ሥራዎችን አፈፃፀም እና ባህሪን መነሻ

ባደረገ እና የከርሰ ምድር ጉድጓዱን የአገልግሎት ዘመን ወይም የፕሮጀክት ባህሪ ታሳቢ በማድረግ እና በባለስልጣኑ ጥናት መሰረት የሚወሰን ይወሰናል፤

2. ባለስልጣኑ የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራውን ለመሥራት የሰጠውን የፈቃድ ጊዜ የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራውን ፕሮጀክት ባህሪ እና በሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች መሰረት በማድረግ ሊያራዝም ይችላል፤

17. **<u>ፈቃድ ማስተላለፍ ስለመከልከሉ</u>**

የከርሰ ምድር ውሃ ጉዳጓድ ቁፋሮ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በቅድሚያ ከባለስልጣኑ ፈቃዱ እንዲተላለፍ የፅሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ ፈቃዱን ለማስተላለፍ አይችልም፡፡

18. **<u>የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፈቃድ ስለመሰረዝ</u>**

1. ባለስልጣኑ በሚከተሉት ምክንያቶች  የከርሰ ምድር ቁፋሮ ፈቃድን ሊሰረዝ ይችላል፡-

   ሀ) ባለፈቃዱ የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራውን  ከሚጠበቀው የሙያ ስነምግባር ፤አሰራር ስርአትን እና ይህንን መመሪያ በሚጥስ ሁኔታ መከናወኑ  ሲያረጋግጥ፤

   ለ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘው የሃሰት ማስረጃ በመስጠት መሆኑን ባለስልጣኑ ሲያረጋግጥ፤

   ሐ) የውሃ ሃብቱ ዘለቄታዊ በሆነ መልኩ  እየመነመነ መሆኑን ባለስልጣኑ ሲያረጋግጥ፤

   መ) የባለፍቃዱ የውሃ አጠቃቀም በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማድረጉ ሲረጋገጥ፤

   ሠ) ባለፈቃዱ በተሰጠው የመጠቀሚይ ፍቃድ ማስረጃ ላይ ከተገለጸለት የቀን የውሃ ፍጆታ አንፃር እና በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተሰልቶ የሚገኝ ውጤት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጉድጓድ አናት ላይ በተገጠመ የውሃ ቆጣሪ በሚወስድ ንባብ የሚኖር ልዩነት ከ100% በላይ ከሆነ እና ባለፈቃዱ ለዚህ አጠቃቀም የሚያቀርበው አሣማኝ ማስረጃ ከሌለ፤

   ረ) ባለስልጣኑ ሳይፈቅድ በውሃ የመጠቀም ፈቃድን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤

2. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ማናቸውም መፈፀማቸውን ሲያረጋግጥ የመሰረዝ እርምጃውን ከመውሰዱ በፊት ለባለ ፍቃዱ የአንድ ወር የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

3. ባለፈቃዱ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ግዜ ውስጥ ሁኔታውን ካላስተካከለ ባለስልጣኑ ፈቃዱን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሰረዝ ይችላል፡፡

19. **<u>በቁፋሮ ወቅት ስለሚኖሩ ግዴታዎች</u>**

የሚከተሉት ተግባራት በፈቃድ ያገኙ እና በባስልጣኑ በጋራ የሚከወኑ ተግባራት ይሆናሉ፡-

1. የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድቁፋሮ ሥራውን ለመሥራት በተወሰነው ወይም በተራዘመው የግዜ ገደብ ውስጥ እንዲሰራ የተፈቀደው ሥራ እንደተጠናቀቀ ወይም ከመጠናቀቁ በፊት ወዲያውኑ እንደነገሩ ሁኔታ ፈቃድ ያገኙ ለባለስልጣኑ ሥራው መጠናቀቁን ወይም ይጠናቀቃል ተብሎ የሚጠበቀውን ግዜ በፅሁፍ ማስታወቅ አለበት፤
2. በተገኘ ፈቃድ መሰረት ሥራቸው ለተጠናቀቀ ወይም ላልተጠናቀቀ የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራዎች አፈፃፀም የመቆፈር ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሥራው ከተጠናቀቀ ወይም ከተቋረጠበት ግዜ ጀምሮ በ 15 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤
3. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 መሰረት የጽሁፍ ማስረጃ እና ሪፖርት ሲደርሰው እንዳግባብነቱ ሥራው በመሰራት ላይ ያለ ከሆነ ሥራው እየተከናወነ ያለው በፈቃዱ እና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን ገደቦችና ሁኔታዎችን ጠብቆ መሆኑን ይከታተላል፤ ሥራው ተጠናቆ ከሆነም ሥራው የተሰራው በፈቃዱ ውስጥ እና በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፤
4. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ስለሥራው አለመጠናቀቅ ሪፖርት ሲደርሰው ሥራው ያልተጠናቀቀበትን ምክንያት በማጣራት በዚህ መመሪያ መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

20. **<u>ፈቃድ ስለሚከለከልበት ወይም ስለማይሰጥበት ሁኔታ</u>**

1. ባለሥልጣኑ የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፈቃድ ለማግኘት የቀረበ ጥያቄን ለህዝብ ደህንነት ወይም ጥቅም ሲባል፤ ለአካባቢ ጥበቃ ወይም የከርሰ ምድር ውሃ ሃብትን ለመጠበቅ ሲባል፤ ከከተማው የማስተር ፕላን ጋር ተቃርኖ ሲኖር ሊከለክል ወይም ላይሰጥ ይችላል፤

2. የባለስልጣኑ የበላይ ሃላፊ በልዩ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር ለቤት ውስጥ ፍጆታ ለማዋል ወይም በከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ባልሆነ ደርጅት/ተቋም ለሚያቀርብ የጉድጓድ ቁፋሮ ጥያቄ ፈቃድ አይሰጥም፡፡

3. በፈቃድ ጠያቂው ይዞታ አካባቢ በባለሥልጣኑም ሆነ በሌላ ሶስተኛ በህጋዊ ሁኔታ የለማ የውሃ ጉድጓድ በመኖሩ ምክንያት በባለስልጣኑ መስፈረት እና ግምገማ መሰረት ፈቃዱ ቢሰጥ በዚህ ጉድጓድ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ከታመነበት ፈቃድ ሊከለከል/ላይሰጥ ይችላል፤

4. ባለስልጣኑ ወደፊት በአካባቢው የሚያለማው የከርሰ ምድር ውሃ ፕሮጀክት መኖሩ ሲረጋገጥ እና በባለስልጣኑ መስፈርትና ግምገማ መሰረት ፈቃዱ ቢሰጥ በፕሮጀክቱ ላይ ተፅዕኖ የሚኖረው መሆኑ ሲታመንበት ፈቃድ ላይሰጥ ይችላል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተደነገገው ቢኖርም፡-

   ሀ) ለመንግስት ተቋማት፣ ለልማት ድርጅቶች፣ ለሆስፒታሎች፣ለትምህርት ቤቶች፣ ለከፍተኛ ኢንደስትሪዎች፣ከሶስት ኮከብ በላይ ለሆኑ ሆቴሎች፣ የሪል እስቴት አልሚዎች እና ለመንግስት የልማት ሥራዎች ተቋማቱ የሚያቀርቡትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ እና በአካባቢያቸው ያለውን የግልም ሆነ የመንግስት የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ወይም ሌላ የመሰረተ ልማት ላይ ችግር የማይፈጥር የውሃ ጉድጓድ ቁፍሮ ቴክኒክ እንዲጠቀሙ በማድረግ እንዲሁም ለሚፈጠር ማንኛውም ችግር ኃላፊነት እንዲወስዱ ግዴታ በማስገባት ፈቃዱ ሊሰጥ ይችላል፤

   ለ) ባለ 2 እና 3 ኮከብ ሆቴሎች፣ መካከለኛ የግል ኢንዱስትሪዎች ፣ኢንባሲዎች፣ ከፍተኛ ውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች በ250 ሜትር ራዲየስ ውስጥ ሌላ የግልም ሆነ የመንግስት የውሃ ጉድጓድ ከሌለ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል፤

21. **<u>የጥንቃቄ እርምጃዎች</u>**

የከርሠ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፍቃድ አሰጣጥ፣ አሰራር እና የጥንቃቄ እርምጃዎችን በተመለከተ የሚከተሉት ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል፡-

1. በከተማው ክልል ውስጥ ህጋዊ በሆነ አግባብ የከርሠ ምድር ውሃ ጉድጓድ አልምቶ እየተጠቀመ ባለ ግለሰብ በቅርብ ርቀት የቁፋሮ ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብ ፈቃድ የሚሰጠው የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በባለስልጣኑ ውስጥ ባሉ መረጃዎች እና በግለሰቦች ወይም በድርጅቶች ወቅታዊ አጠቃቀም ሁኔታ አንፃር ተጣርቶ እና ተተንትኖ ይሆናል፤

2. አዲስ ፈቃድ የሚሠጠው የፍቃድ ጠያቂው የውሃ አጠቃቀም ሁኔታ ቀድመው በማልማት እየተጠቀሙ ባሉ ግለሠቦች ወይም ድርጅቶች ላይ የነጠላ ወቅታዊ የእለት የውሃ ፍጆታ አንፃር እስከ ግማሽ የውሃ መጠን ቢጠቀም ቀድመው በማልማት ጥቅም ላይ እያዋሉ ባሉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ችግር የማያስከትል መሆኑን ሲያረጋግጡ ነው፤

3. የከርሠ ምድር ውሃ ቁፋሮ ጥያቄ አቅራቢው በተደረገው የቅድመ ምርመራ መሰረት ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፁት ሁኔታዎች እንዲሁም በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ 5 እስከ 14 ያሉት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ፈቃድ ጠያቂው አገልግሎቱን ለማግኘት በቅድሚያ አግባብነት ያላቸውን የሮያሊቲ እና የአገልግሎት ክፍያውን መፈፀም ይኖርበታል፤

4. በከተማው ክልል ውስጥ ህጋዊ በሆነ አግባብ ፈቃድ ተሠጥቷቸው በማልማት እየተጠቀሙ ያሉ ግለሠቦች ወይም ድርጅቶች በቅርብ ርቀት ለህዝብ ጥቅም ሲባል ባለስልጣኑ የከርሠ ምድር ውሃ ለመቆፈር ሲያስብ አልምተው እየተጠቀሙ ያሉ ግለሠቦች ወይም ድርጅቶችን ጠርቶ በማነጋገር ጥቅማቸውን የማይጎዳ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፤

5. በዚህ መመሪያ አንቀጽ (20) ንኡስ አንቀጽ (10) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ የሚቆፈረው የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ በአካባቢው የከርሰ ምድር ውሃን አልምተው በመጠቀም ላይ ያሉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የከርሠ ምድር ውሃ አጠቃቀም ላይ ችግር የሚፈጥር መሆኑ ሲረጋገጥ፡-

   ሀ) ባለስልጣኑ በመስመር ከሚሠጠው የውሃ አገልግሎት በተጨማሪ የከርሰ ምድር አልምቶ እየተጠቀመ የነበረው ግለሰብ ወይም ድርጅት ከከርሰ ምድር የጉድጓድ ውሃ መገኛ ያገኝ የነበረውን የቀን የውሃ ፍጆታ መጠን ያክል እንዲሠጠው ያደርጋል፤

   ለ) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ተራ ፊደል (ሀ) በተቀመጠው መሰረት ህጋዊ በሆነ አግባብ ቀድሞ አልምቶ በመጠቀም ላይ ያለን ግለሰብ ወይም ተቋም ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የማይችል ሆኖ ሲገኝ ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ የከርሠ ምድር ውሃ ጉድጓድ መገኛውን ለማልማት ያወጣውን ወጭ የሚያረጋግጥ ሠነዶች ሲያቀርብ ያወጣውን ወጪ የከርሰ ምድር ውሃውን መጠቀም ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አገልግሎቱ ሊቋረጥ እስከሚችልበት ጊዜ ድረስ የየዕለቱ የውሃ ፍጆታ በወቅቱ ባለሥልጣኑ በሚጠቀመው የጉድጓድ

ውሃ ታሪፍ ተባዝቶ በሚገኘው ስሌት መሠረት የማይሸፈን ወጪ መኖሩ ሲረጋገጥ ልዩነቱ ላለማው ግለሠብ ወይም ድርጅት በካሣ መልክ ይሠጣል፤

## ክፍል ሦስት

## ፈቃድ ስለማገድ፣ስለማሻሻልና እና እድሳት

### 22. የከርሰ ምድር ጉድጓድ ውሃ የመጠቀም ፍቃድ ስለማገድ

1. ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ምክንያቶች ባለስልጣኑ የተሰጠ ፈቃድን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ሊያግድ ይችላል፡-
   ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተቀመጡ ግዴታዎችንና ገደቦችን አለመጠበቅና አለማክበር፤
   ለ) ውሃን ከተፈቀደው አገልግሎት ውጪ መጠቀም፤
   ሐ) የውሃ ጥራት ደረጃዎችን አለመጠበቅ፤
   መ) የውሃ ሃብቱ በግዜያዊነት እየመነመነ መሆኑን ባለስልጣኑ ሲያምን፤
   ሠ) የውሃ ግልግሎት ዋጋን የአገልግሎት ክፍያ ማሳወቂው በደረሰ በ30 ቀናት ውስጥ አለመክፈል፤
   ረ) የቀጥታው መስመር የውሃ ፍጆታ እዳ እንዳለበት ተረጋግጦ ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆኑ ከሚመለከተው ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ወይም ክፍል ማረጋገጫ ሲቀርብ፤
   ሰ) የፍሳሽ ቆሻሻ ህጋዊ በሆነ አግባብ በፍሳሽ መስመር የሚያስወገድ ከሆነ እና ህገወጥ ድርጊት የፈፀመ መሆኑ ከሚመለከተው ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ወይም ክፍል ማረጋገጫ ሲቀርብ፤
   ሸ) ለምቶ ጥቅም ላይ እየዋለ ባለ የጉድጓድ ውሃ መገኛ ላይ ለባለስልጣኑ ሳያውሳውቅ እና ፍቃድ ሳያገኝ የተለያዩ የማሻሻያ የለውጥ ሥራዎችን መሥራቱ ሲረጋገጥ፤
   ቀ) ሌሎች በባለሥልጣን መስሪያ ቤት በኩል የሚሠጡ ማናቸውንም አገልግሎቶችን አግኝቶ የአገልግሎት ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር እና ከሚመለከተው ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ወይም ክፍል ሲረጋገጥ እንዲሁም በህገወጥ ድርጊት ላይ ሲሳተፍ በቀረበ ማረጋገጫ ለመውሰድ ህጋዊ የማስተካከያ ርምጃ ተባባሪ አለመሆኑ ከሚመለከተው ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ወይም ክፍል ሲረጋገጥ፤
2. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ማናቸውም መፈፀማቸውን ሲያረጋግጥ የእግድ እርምጃውን ከመውሰዱ በፊት ለባለ ፍቃዱ የአንድ ወር የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

3. ባለፈቃዱ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ግዜ ውስጥ ሁኔታውን ካላስተካከለ ባለስልጣኑ ፈቃዱን በከፊል ወይም በሙሉ ማገድ ይችላል፡፡

23. **የከርሰምድር ውሃ ጉድጓድ የአጠቃቀም ፈቃድ ስለማሻሻልና ማስተላለፍ**

1. ፈቃድ ያገዠ የተፈቀደለት የውሃ መጠን እንዲቀነስለት ወይም እንዲጨመርለት ወይም ውሃውን ጠቀሜታ ላለው ሌላ ተግባር እንዲያውል ፈቃዱ እንዲሻሻልለት ሊያመለክት ይችላል፤
2. ባለስልጣኑ ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው ማመልከቻ ሲቀርብለት በ 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥበታል፤
3. ባለስልጣኑ የአካባቢ ሁኔታዎች በመለዋወጣቸው ወይም በውሃ ለመጠቀም ያለው ፍላጎት በመጨመሩ ወይም በማናቸውም ሌላ በቂ ምክንያት የውሃውን ክፍፍል እንደገና ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ይህንኑ ለፈቃድ ያገዠ ከ 90 ቀናት በፊት በፅሁፍ በማስታወቅ ፈቃዱን ሊያሻሽል ይችላል፤
4. ፈቃድ ያገዠ የውሃ መጠቀም ፈቃዱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲተላለፍለት ወይም በጋራ ለመጠቀም ሲፈልግ ጥያቄውን አቅርቦ ባለስልጣኑ ሲፈቅድ በውሃ ሃብት የመጠቀም ፈቃድ ለሌላ ሰው ሊተላለፍ ይችላል፤ ይህም በፈቃድ ያዥ በኩል ጥያቄው ቢቀርብ በኋላ በሚኖር 30 ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፤
5. ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (4) በተገለፀው መሰረት የውሃ መጠቀም ፈቃድ እንዲለወጥለት ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲተላለፍለት ፈቃድ ያገዠ ለባለስልጣኑ የሚያቀርበው ማመልከቻ በውሃ የመጠቀም ፈቃዱ እንዲለወጥ ወይም እንዲተላለፍ የተፈለገበትን ምክንያትና መለወጡን ወይም መተላለፉን ለመፈፀም እንዲሟሉ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎችና ገደቦች መግለፅ አለበት፡፡

24. **የፈቃድ ጊዜ እና እድሳት**

የከርሠምድር ውሃ ጉድጓድ መጠቀሚያ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜና የሚታደስበት ሁኔታእንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. ባለሰልጣኑ ለሚቀርበው በከርሰ ምድር ውሃ የመጠቀም ጥያቄ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር አንድ አመት ጊዜ ብቻ ነው፤
2. ባለፈቃዱ የመጠቀሚያ ፈቃዱ የአንድ ዓመት ግዜ ሊጠናቀቅ ሶስት ወራት ሲቀሩት የመጠቀሚያ ፈቃዱ እንዲታደስለት ጥያቄውን በፅሁፍ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፤
3. የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ሲቀርብ ባለስልጣኑ ፈቃድ ያገዠ በፈቃዱ ውስጥ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች፣ ግዴታዎችና ገደቦች እንዲሁም በባለሰልጣኑ ማቋቋሚያ

አዋጅ ፣ደንብ እና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን አስፈላጊ ሁኔታዎች ማክበሩን ሲያረጋግጥ የፈቃድ እድሳት ጥያቄው በቀረበለት በ 15 ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለተጨማሪ አንድ አመት ያድሳል፤

4. ባለፍቃድ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) በተቀመጠው የግዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱ እንዲታደስለት ጥያቄ ካላቀረበ ወይም ጥያቄውንም አቅርቦ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ባለስልጣኑ ፈቃዱን ካላደሰለት ፈቃዱ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤
5. ፈቃድ ያኘ ፈቃዱ እንዲታደስለት ሲመጣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለን የውሃ መጠን በጉድጓድ አናት ላይ በተገጠመ የውሃ ቆጣሪ ንባብ እና በወቅቱ በሚኖር የጉድጓድ ውሃ ታሪፍ ስሌት ተባዝቶ በሚገኘ ውጤት በባለስልጣኑ ደንብ በተገለጸው ታሪፍ መሰረት ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፤
6. ፈቃድ ያኘ ፈቃድ እንዲታደስለት ሲመጣ ሁለት ሊትር ውሃ ናሙና ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤ የቀረበን የናሙና ውሃ የላብራቶሪ ውጤት መነሻ በማድረግ የአጠቃቀም ፍቃድን በነባሩ ሊያስቀጥል ወይም ሊቀየር ይችላል፡፡

25. <u>ስለ የአቅም ፍተሻ እና ሪፖርት</u>

1. የከርሰምድር ውሃ አጠቃቀም ፈቃድ ጠያቂው የሚያስቆፍረው ጉድጓድ የቁፋሮ ሂደት ተጠናቆ የጉድጓድ ቁፋሮ የአቅም ፍተሻ በሚደረግበት ዕለት የባለስልጣኑ ባለሙያዎች እንዲገኙ የጉድጓድ ቁፋሮ የአቅም ፍተሻ የሚደረግበትን ግዜ ጠቅሶ በፅሁፍ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች የመስክ ላይ ማረጋገጫ እንዲሰጡ ማድረግ አለበት፤ ሆኖም ጉድጓድ ያስቆፈረው ሰው የባለስልጣኑ ባለሙያዎች እንዲገኙ አሳውቆ የባለስልጣኑ ባለሙዎች በተለያየ ምክንያት በመስክ ላይ ሳይገኙ ቢቀር የጉድጓድ አቅም ፍተሻው ለማከናወን ይችላል፤
2. ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም የከርሰ ምድር ጉድጓዱን ያስቆፈረው ሰው የከርሰምድር ውሃ አጠቃቀም ፈቃድ ለማግኘት በከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ አቆፋፈር ስልት ወይም አሰራር መሰረት የተሟላ ይዘት ያለው ሥራውን ባከናወነው ድርጅት የተረጋገጠ እና ህጋዊ ማህተም ያረፈበት የጉድጓድ ቁፋሮ ዊል ኮምፖሊሽን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፤
3. ባለስልጣን የአጠቃቀም ፍቃድ ከመስጠቱ በፊት የውሃ ጉድጓዱ ከተቆፈረበት ስፍራ ላይ በመገኘት የውሃ ናሙና በመውሰድ የላብራቶሪ ፍተሻ ያደርጋል፡፡ወጪውንም ባለቤቱ የሸፍናል፡፡

26. <u>ዕለታዊ የከርሠ ምድር ውሃ ምርት መጠን ስለመወሰን</u>

1. ከላይ በዚህ መመሪያ የተጠቀሰውን መስፈርቶች በማሟላት የከርሰ ምድር ውሃ አጠቃቀም ፈቃድ የተሰጣቸው አልሚዎች ዕለታዊ የውሃ ምርት መጠናቸው የሚወሰነው በባለስልጣኑ ሆኖ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡-

   ሀ) አልሚው ሰው በሚያቀርበው የተሟላ ይዘት ባለው የጉድጓድ ቁፋሮ ኮምፖሊሽን ሪፖርት፤

   ለ) በአልሚው ሰው የለማው የከርሰምድር ውሃ የውሃ ናሙና ጥራት ፍተሻ ውጤት መነሻነት በማድረግ ባለሥልጣኑ አረጋግጦ በሚሠጠው የአጠቃቀም ትዕዛዝ መነሻ፤

   ሐ) አልሚው በሚያቀርበው ለአገልግሎቱ ጥቅም ላይ ሊያውል የሚፈልገውን የተጠና የቀን የውሃ ፍጆታ ሪፖርት፤

   መ) ፈቃድ ጠያቂው ሰው ባስቆፈረው ይዞታ አካባቢ በሌሎች ቀድመው መሠል ልማት ባከናወኑ ሰዎች እና በባለስልጣኑ በራሱ ለምተው አገልግሎት እየሠጡ ያሉ የከርሠ ምድር ጉድጓድ ውሃ መገኛዎችን የጉድጓድ ቁፋሮ ኮምፖሊሽን ሪፖርት ፣የአጠቃቀም  እና ወቅታዊ የውሃ ምርት ሁኔታ ተገናዝቦ በሚገኝ የተፅዕኖ ሪፖርት ውጤት ፤

   ሠ) ፈቃድ ጠያቂው ሰው ባስቆፈረው ይዞታ ዙሪያ ወይም አካባቢ ያለውን የከተማውን ማስተር ፕላን መነሻ ያደረገ የቀጣይ የአካባቢ ልማት ምክንያት ሊገጥም የሚችልን የአካባቢ የውሃ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፤

   ረ) ከባለስልጣኑ በቀጥት የውሃ መስመር በቆጣሪ የሚያገኝ ከሆነ የተቆፈረ አማራጭ የጉድጓድ ውሃ መገኛው ለምቶ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት የነበረ ወደ ኋላ የሦስት ወር የውሃ አጠቃቀም በቢል በሚወሰድ ዳታ ተሰልቶ እና ወደ ቀን የውሃ ፍጆት ስሌት ተቀይሮ በሚገኝ መረጃ፤

   ሰ) የቁፋሮ ጥናት የቀን የውሃ ፍጆታ በባለስልጣኑ በኩል በቀጥታ የውሃ መስመር በውሃ ቆጣሪ እየተሰጠ ከነበረ የቀን የውሃ መጠን አንፃር ተቀናንሶ የሚገኘው ከአቅርቦት አንፃር የፍላጐት ጥናት መነሻ የውሃ አጠቃቀም ከፍቃድ ጠያቂው ቀድሞ የለማ የሌሎች ሰውወይም የባለሥልጣኑ የጉድጓድ ውሃ መገኛ ካለ የሚሰጠው የውሃ አጠቃቀም የውሃ መጠን ያነሰ ሊሆን ይችላል፤

2. ከላይ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው ቢኖርም ባለስልጣኑ የዜጎችን ፍትሃዊ  የጋራ ሃብት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ቀድመው የተሠጡ ዕለታዊ የከርሠ ምድር ውሃ ምርት መጠን ፈቃዶችን ለአልሚ ሰው በማሣወቅ የዕለታዊ የከርሠ

ምድር ውሃ ምርት መጠን ፈቃዶች ላይ ማሻሻያዎችን የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ አያያዝ፣ የውሃ ጥራት ምርመራ እና አካባቢ ጥበቃ

### 27. የከርሰ ምድር ውሃ ጥራት ምርመራ እና ውሃ አጠቃቀም

1. የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ሥራ ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት የጉድጓዱ ውሃ ናሙና በባለስልጣኑ ላብራቶሪ ቀርቦ የውሃ መጠቀሚያ ፈቃድ ጠያቂው በማመልከቻው ላይ ለጠየቀው አገልግሎት ሊውል የሚችል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤
2. ማንኛውም ከርሰ ምድር ውሃ አቅርቦት ጉድጓድ ጠረጋ ሥራ ከተከናወነ በኋላ ከጉድጓዱ እድሜ አንፃር ወይም በጠረጋው ሥራ ምክንያት በውሃው ጥራት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የባክቴሪዮሎጂካልና የኬሚካል ለውጦች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ የጉድጓዱ ውሃ ናሙና በባለስልጣኑ ላብራቶሪ ቀርቦ ምርመራ መደረግ አለበት፤
3. የከርሰ ምድር ውሃ መጠቀም የሚቻለው የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ሥራ እና የከርሠ ምድር ውሃ ጉድጓድ የአቅም ፍተሻው በሚጠናቀቅበት እለት ወይም የአጠቃቀም እድሳት ጥያቄ በሚቀርብበት እለት ሁለት ሊትር የውሃ ናሙና በመያዝ በባለስልጣኑ ላብራቶሪ የውሃ ጥራት ምርመራ በማስመርመር በሚገኘው የፍተሻ ውጤት ሪፖርት መሠረት ብቻ ነው፤
4. በባለሰልጣኑ የውሃ ጥራት ላብራቶሪ ምርመራ በተገኘ የፍተሻ ውጤት መሠረት ከተፈቀደ አገልግሎት ውጪ ውሃውን ላልተፈቀደ አገልግሎት ያዋለ ማንኛውም የውሃ መጠቀሚያ ባለፈቃድ ውሃውን ላልተፈቀደ አገልግሎት በማዋሉ ለሚፈጠረው ማንኛውም ችግር በኃላፊነት ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ መሰረት እርምጃ ይወስዳል፤
5. የአጠቃቀም ፈቃድ ለማግኘትም ይሁን የአጠቃቀም ፈቃድ እድሳት ለማግኘት ለሚቀርብ እና ለሚደረግ የውሃ ናሙና ምርመራ ሥር በወቅቱ በሚኖር የባለስልጣኑ የአገልግሎት የክፍያ ታሪፍ መነሻነት ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## 28. የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓዶች አያያዝ እና  አካባቢ ጥበቃ

ማንኛውም የከርሰ ምድር ውሃ ጉዳጓድ ቁፋሮ ወይም የከርሰ ምድር ውሃ የመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው የቁፋሮ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ሥራው የከርሰ ምድር ውሃን እና የውሃ አካላት እንዳይበክል እንዲሁም በሰው፣ በእንስሳት እና በአካባቢላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡-

1. ጉድጓዱ በእጅ ፐምፕ የሚሰራ የውሃ ጉድጓድ ከሆነ ጉድጓዱ የውሃ ብክለትን ሊያስከትል እንደሚችል ከታወቀ ወይም ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ከሚገመት በካይ ነገር ቢያንስ 30 ሜትር መራቁን ማረጋገጥ፤
2. ጉድጓዱ በሜካናይዝድ ፐምፕ የሚሰራ የውሃ ጉድጓድ ከሆነ ጉድጓዱ የውሃ ብክለትን ሊያስከትል እንደሚችል ከታወቀ ወይም ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ከሚገመት በካይ ነገር ቢያንስ 50 ሜትር መራቁን ማረጋገጥ፤
3. የጉድጓዱ ኬዚንግ ከመሬት በላይ ቢያንስ ከ 0.5 ሜትር መሆኑን ወይም የተጠናቀቀው የፓምፕ ቤቱ  ወለል በአግባቡ መሰራቱንና መጠገኑን እንዲሁም የፓምፕ ቤቱ ወለል ወደ ጉድጓዱ ውሃ የማያሰርግ መሆኑን መከታተልና ማረጋገጥ፤
4. ማንኛውም ከከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ እና ከውሃ ሥራዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለት እንዳይከሰት ለመከላከል ያወጣቸውን መመሪያዎችና የሚሰጣቸውን የአካባቢ ጥበቃ ትዕዛዞች ባከበረ ሁኔታ ማከናወን እና መከናወናቸውን የማረጋገጥ፤
5. ማንኛውም የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ በቁፋሮ በግንባታ ወቅት በሚያጋጥሙ ችግሮች ፤በቁፋሮ ሂደት ላይ  እያለ የተቆፈረው ጉድጓድ ቢመክን ወይም  ተንዶ ወይም  ጉድጋዱ ውስጥ  በዓድ ነገር ገብቶ  መሥራት ባይቻል  ወይም በብክለት ስጋት  ቁፋሮው እንዲቆም ሲደረግ ፈቃድ ያገኙ ጉድጓዱን በአግባቡ መድፈን እና ካፕ በማድረግ ከባለስልጣኑ  በአግባቡ  ስለመደፈኑ  ህጋዊ ሰርቲፊኬት መውሰድ፤
6. ባለስልጣኑም ጉዳዩን በአካል መርምሮ  ማስተካከያ ካስፈለገ  ፈቃድ ያገኙ እንዲፈጽም በማድረግ  ሲሰተካከል  ጉድጋድ ደፈናው  ስርቲፊኬት  በአግባቡ መሰረት  መከናወኑን  የሚረጋግጥ  ሰነድ  ለፈቃዱ  ያገኙ ሊሰጠው ይገባል፤ ፍቃድ ያገኙም የተደፈነው ጉድጓድ ቁፋሮ ታሪክ  ሙሉ ሪፖርት ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፤
7. የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓዶች ውስጥ ማንኛውም በካይ ፍሳሽ ሰርጎ እንዳይገባ በጉድጓዱ ቀፎና በጉድጓዱ መካከል ያለ ክፍት ቦታ መታሸግ አለበት፤

8. የጉድጓድ ውሃውን የከርሠ ምድር የውሃ አካላት ብክለት እንዳይደርስባቸው ከመሬት በታች 30 ሜትር ድረስ ጥንቃ በተሞላበት አግባብ በሲሚንቶ ግሩት መደረግ አለበት፤
9. ማንኛውም ከከርሠምድር ውሃ ቁጥሮ እና ከውሃ ሥራዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች በይዞታው ላይ ወይም በይዞታው ዙሪያ ያሉ ግንባታዎች ላይ በቁፋሮ ሂደትም ይሁን በአቀጠቃቀም ወቅት ሊፈጠሩ የሚተሉ አደጋዎችን ለመከላከል ሲባል የግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር ባለሥልጣን ያወጣቸውን መመሪያዎችና የሚሠጣቸው ትዕዛዞች ባከበረ ሁኔታ ማከናወን እና መከናወናቸውን ማረጋገጥ፤
10. የጉድጓድ ተጠቃሚነት ፈቃድ ያለው በየጊዜው የጉድጋዱን የውሃ አጠቃቀም ታሪክ ሪኮርድ ሳይቆራረጥ በተደራጀ መልኩ በጽሁፍ መያዝ ይኖርበታል፤
11. ባለስልጣኑም ወጥነት እንዲኖረው የአጠቃቀም ፎርማት አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ያቀርባል፤
12. የፈቃድ እድሳት ሲደረግ ፍቃድ ያዡ የአመቱን አጠቃቀም ሪፖርቱን በጽሁፍ ያቀርባል፡፡

29. **<u>የጠረጋ ፈቃድ</u>**

1. ፈቃድ የተሰጠው ሰው የከርሰ ምድር ውሃ ጥራት ሲቀየር ወይም ሲቀንስ ጥራቱን ወይም የውሃውን መጠን ለማስተካከል የከርሰ ምድር ውሃ የጠረጋ ፈቃድ እንዲሰጠው ባለስልጣኑን ለመጠየቅ ይችላል፤ ባለስልጣኑም የቀረበው የከርሰ ምድር ውሃ የጠረጋ ፈቃድ ጥያቄ አግባብ መሆኑን ካመነበት ፈቃዱን ለጠያቂው ለመስጠት ይችላል፤
2. ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ባለስልጣኑ የከርሰ ምድር ውሃ የጠረጋ ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ በይዞታው ስር ያለውን የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ የጠረጋ ሥራ አፈፃፀም አስመልክቶ በከርሰ ምድር ውሃ ሃብት ቁፋሮ፣አያያዝ እና አጠቃቀም ዙሪ ህጋዊ እውቅና ባለው ተቋም ወይም ባለሙያ የተረጋገጠ የጥናት ሰነድ ማቅረብ አለበት፤
3. የጠረጋ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሥራውን በፈቃዱ ደብዳቤ ላይ በተሰጠው ግዜ ሰሌዳ መሰረት ሥራውናን አጠናቆ መጨረስ አለበት፤ ባለፈቃዱ በተሰጠው የግዜ ሰሌዳ ውስጥ ሥራውን ለማጠናቀቅ ወይም ለመጀመር ካልቻለ ሥራውን ያላጠናቀቀበት ወይም ያልጀመረበት አስገዳጅ እና አሳማኝ ምክንያት በማቅረብ ፈቃዱ እንዲራዘምለት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

4. ባለፈቃዱ በተሰጠው የፈቃድ ግዜ ውስጥ ሥራውን አከናውኖ ካልጨረሰ እና ፈቃዱም እንዲራዘምለት ካልጠየቀ የፈቃድ ግዜው ካበቃ በኋላ ማንኛውንም ሥራ ማከናወን አይችልም፤
5. የጠረጋ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የጠረጋ ሥራውን ካከናወነ በኋላ የጉድጓዱን አቅም ፍተሻ ሥራ የሚያከናውንበትን ቀን ለባለስልጣኑ በማሳወቅ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በቦታው ተገተኝተው እንዲያረጋግጡ ማድረግ አለበት፤ ባለ ፈቃዱ የፍተሻ ግዜውን አሳውቆ የባለስልጣኑ ባለሙያዎቹን ሳይልክ ከቀረ ባለፈቃዱ ፍተሻውን ማከናወን ይችላል፤
6. የጠረጋ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የጠረጋ ሥራውን ካከናወነ እና የጉድጓዱን አቅም ፍተሻ ሥራ ከፈፀመ በኋላ ለውሃ ጥራት ምርመራ በተቀመጡ የአሰራር መመሪያዎች መሰረት የጉድጓዱን የውሃ ጥራት ማስመርመር ይኖርበታል፡፡
7. የጠረጋ ፈቃድ የተሠጠው ሰው የጠረጋ ሥራውን ጨርሶ የአቅም ፍተሻውን ሲጨርስ የሚገኝን ውጤት መነሻ ያደረገ የቀጣይ አጠቃቀም ምክረ ሃሳብ ያካተተ የማጠቃለያ ሪፖርት ህጋዊ እውቅና ባለው ተቋም ወይም ባለሙያ የተረጋገጠ ሠነድ መቅረብ አለበት፤
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) መሰረት የሚቀርብን ሪፖርት መነሻ ያደረገ የአጠቃቀም ፈቃድ በባለሥልጣኑ በኩል ሲፈቀድ ባለፈቃዱ መጠቀም ይችላል፡፡

30. <u>ስለ ፓምፕ ቅየራ</u>

በከርሠምድር ውሃ ጉድጓድ ውስጥ የገባን ጠላቂ ፓምፕ ብልሽት ሲገጥም አውጥቶ የመቀየር የማስተካከል ፈቃድ የሚሰጠው በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል፡-

1. የመጠቀም ፈቃድ የተሠጠው ፈቃድ ያዥ ሰው በከርሠምድር ውሃ ጉድጓድ ውስጥ የገባው ጠላቂ ፓምፕ ብልሽት ገጥሞት ብልሽቱ በባለሙያዎች ተፈትሾ በጉድጓድ ውስጥ የገባው ጠላቂ ፓምፕ ወጥቶ በአዲስ የመተካት ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው ባለሥልጣኑን ሊጠይቅ ይችላል፤ ባለሥልጣኑም የቀረበው ፈቃድ ጥያቄ አግባብ መሆኑን ካመነበት ፈቃዱን ይሰጣል፤
2. የመጠቀም ፈቃድ የተሠጠው ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ በከርሠምድር ውሃ ጉድጓድ ውስጥ የገባን ጠላቂ ፓምፕ ብልሽት ለማስተካከል ፓምፕ አውጥቶ በአዲስ የመቀየር ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ በጉድጓድ ውሃ መገኛው የገባው ፓምፕ የገጠመው የብልሽት ዓይነት፣ ብልሽቱን ለማስተካከል መወሰድ ስላለበት የማስተካከያ ርምጃ እና እንዴት እንደሚፈፀም ዝርዝር ጥናት ህጋዊ እውቅና ባለው ተቋም ወይም ባለሙያ የተረጋገጠ የጥናት ሠነድ መቅረብ አለበት፤

3. ብልሽት የገጠመውን የጠላቂ ፓምፕ አውጥት የማስገባት ፈቃድ የተሠጠው ሰው ሥራውን በፈቃድ ደብዳቤ ላይ በተሠጠው ጊዜ ሠሌዳ መሠረት ሥራውን አጠናቆ መጨረስ አለበት፤ በተሠጠው ጊዜ ሠሌዳ ውስጥ ሥራውን ለማጠናቀቅ ወይም ለመጀመር ካልቻለ ሥራውን ያላጠናቀቀበት ወይም ያልጀመረበት አስገዳጅ እና አሳማኝ ምክንያት በማቅረብ ፈቃዱ እንዲራዘምለት ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፤
4. ባለፈቃዱ በተሠጠው የፈቃድ ጊዜ ውስጥ ሥራውን አከናውኖ ካልጨረሰ እና ፈቃዱም እንዲራዘምለት ካልጠየቀ የፈቃድ ጊዜው ካበቃ በኋላ ማንኛውንም ሥራ ማከናወን አይችልም፤
5. ብልሽት የገጠመውን የጠላቂ ፓምፕ አውጥቶ የማስገባት የማስተካከያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የማስገባት ሥራው አከናውኖ የፍተሻ ሥራ በሚያከናውንበት ቀን ለባለሥልጣኑ በማሳወቅ የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች በቦታው ተገኝተው እንዲያረጋግጡ ማድረግ አለበት፤ባለ ፈቃዱ የፍተሻ ጊዜውን አሳውቆ ባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ሳይልክ ከቀረ ባለፈቃዱ ፍተሻውን ማከናወን ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ተግባርና ኃላፊነት

31. የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

ባለስልጣኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. በአካባቢው ስለሚገኘው አማራጭ የከርሰ ምድር የውሃ መገኛ መረጃ እና የምክር አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት አለበት ለሚሰጠው አገልግሎትም አግባብ ባለው ህግ መሰረት አስፈላጊውን ክፍያ ያስከፍላል፤
2. በከተማ ክልል ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ለምተው አገልግሎት በመሥጠት ላይ ያሉ እና በመልማት ላይ ያሉ የከርሠ ምድር ውሃ መገኛ ጉድጓዶች ዝርዝር መረጃ በካርታ ጭምር የተመላከተ ዳታ በሃርድ እና ሶፍት ኮፒ አደራጅቶ በመያዝ በየጊዜው የሚኖሩ ለውጦችን በመከታተል መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል፤
3. የከርሰ ምድር ውሃ አልሚ ስለ ውሃ አጠቃቀምና ማጣራት ሂደት የምክር አገልግሎት ሲፈልግና ሲጠይቅ አግባብ ባለው ህግ መሰረት አስፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል አገልግሎቱን ይሰጣል፤

4. የከርሰ ምድር ውሃ አልሚ የውሃ ጥራት ቁጥጥር ለማድረግ ሲፈልግና ሲጠይቅ አግባብ ባለው ህግ መሰረትአስፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል የላብራቶሪ አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት አለበት፤
5. የከርሰ ምድር ውሃ አልሚ ያጎለበተው የውሃ ምንጭ ችግር ሲገጥመው አግባብ ባለው ህግ መሰረት አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል የጥገና ባለሙያ በመመደብ የገጠመውን ችግር አይነት የመፈተሽ ፣ የመለየት እና የማሳወቅ እንዲሁም የገጠመውን ችግር በመለየት የጥገና አገልግሎት ድጋፍ ለመስጠት ይችላል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) መሰረት ያጋጠመው ብልሽት የተተከለ ጠላቂ ፓምፕ እና ሞተር እንዲሁም ተያያዥ መሳሪዎችን አውጥቶ በማየት ፣ችግሩን በመፈተሽ የመለየት ፣ውጤቱን የማሳወቅ እና የማስተካከያ እርምጃው ጠላቂ ፓምፕና ሞተር እንዲሁም ተያያዥ መሳሪያዎችን የመቀየር ወይም የመተካት የተከላ ሥራ ከሆነ የባለስልጣኑ ወቅታዊ የመፈፀም አቅምን መነሻ ያደረገ የተከላ እና የጥገና አገልግሎት ክፍያአግባብ ባለው ህግ መሰረት በማስፈፀም አገልግሎቱን ሊሰጥ ይችላል፤ ለአገልግሎቱም የአንድ ወር የሥራ ዋስትና ይሰጣል፤
7. የከርሰ ምድር ውሃ አጎልብተው በመጠቀም ላይ ያሉ አልሚዎችን የአጠቃቀም ሁኔታ የመከታተል ፣የመቆጣጠር እንዲሁም የመደገፍ ሃላፊነት አለበት፤
8. የከርሰ ምድር ውሃ አልሚ የውሃ ምንጭ በተለያየ ችግር ምክንያት አገልግሎት መስጠት ሲያቆም በማጣራት ባለስልጣኑ ከገነባው ወይም ከሚያቀርበው አማራጭ የውሃ ምንጭ መገኛ ደንበኛው እንዲጠቀም የማመቻቸት ሃላፊነት አለበት፤
9. ማንኛውም የከርሰ ምድር ውሃ አልሚ የጉድጓድ ወይም ማንኛውንም አማራጭ የከርሰ ምድር ውሃ የማጎልበት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከባለስልጣኑ ፈቃድ እንዲያገኝ ያደርጋል፣ ሥራው ተጀምሮ ከሆነም ደንበኛው ፍቃድ የተሰጠው መሆን አለመሆኑን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
10. አማራጭ የከርሠምድር ውሃ ምንጭ በመቆፈር፣ በማጎልበት እና በመገንባት ሂደት የሚፈጠር አካባቢያዊ ተፅእኖዎችን በተመለከተ በአልሚው ግለሠብ/ድርጅት በኩል ተጠንቶ የሚቀርብ ሠነድ በመመርመር ያፀድቃል፤
11. ባለስልጣኑ ለአማራጭ የከርሰ ምድር ውሃ ምንጭነት የሚጎለብቱ የውሃ ምንጮችን የውሃ ጥራት ደረጃ እንዲሁም ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ለተጠቃሚው ወይም የከርሰ ምድር ውሃ አልሚ የማሳወቅ ሃላፊነት አለበት፤

12. በከተማው ክልል ውስጥ ባሉ ቦታዎች ያለን የከርሠ ምድር ውሃ ሃብት ሁኔታ ፣ በሰዎች እንዲሁም በባለስልጣኑ ለምተው አገልግሎት እየሠጡ ያሉ እና በተለያዩ ምክንያት አገልግሎት መሥጠት ያልቻሉ የከርሠ ምድር ውሃ ጉድጓድ መገኛዎች ጋር የተናበበ ዝርዝር ጥናት በአማካሪ በማስጠናት የከተማው ክልል የከርሠ ምድር ውሃ ሃብት ሁኔታን ከመጠን ፣ከጥራት እንዲሁም ከአጠቃቀም አንፃር በማደራጀት መረጃውን ለከተማው ህዝብ እና ለባለድርሻ አካላት ማሳወቅ ሃላፊነት አለበት፤
13. በዚህ መመሪያ መሰረት የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድን ለመቆፈርም ሆነ የከርሰ ምድር ውሃን ለመጠቀም የቀረበን ማመልከቻን አስመልክቶ የሰጠውን ውሳኔ መዝግቦ ይይዛል፤
14. የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ለመቆፈርም ሆነ የከርሰ ምድር ውሃን ለመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት የቀረበን ማመልከቻ በሚያይበት ግዜ አመልካቹ የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ለመቆፈርም ሆነ የከርሰ ምድር ውሃን ለመጠቀም ያቀረበው ጥያቄ የሃገሪቱን የውሃ ፖሊሲ፣የፌደራል የውሃ አስተዳደር ህጎች፣ የከተማውን የተፋሰስ ማስተር ፕላኖች፣ አዋጁን ፣ደንቡን እና ይህን መመሪያ መሰረት ያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፤
15. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (14) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የቀረበውን ማመልከቻ አስመልክቶ የሚሰጠውን ውሳኔ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
16. በከተማው በሚያሰራጨው የውሃ አቅርቦት በድርቅ ወይም በቂ ዝናብ ባለመገኘቱ ወይም በሌላ በቂ ምክንያት የውሃ እጥረት ሲያጋጥመው የአልሚውን የመጠቀም መብት ሳይገድብ ከጎለበተ አማራጭ የውሃ መገኛ ላይ ውሃ በውሃ ቦቴ መኪኖች ወይም በውሃ ማሰራጫ መስመሮች በመጠቀም ውሃውን የመውሰድ መብት አለው፤
17. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (16) መሰረት የከርሰ ምድር ውሃ አልሚው ካለማው የውሃ ጉድጓድ ላይ ለሚወስደው ውሃ አልሚው ከሚከፍለው አመታዊ የሮያሊቲ እና የአገልግሎት ክፍያ ላይ በባለስልጣኑ አሰራር መሰረት ቅናሽ ያደርጋል፡፡

32. <u>**የፈቃድ ጠያቂዎች እና ባለፈቃዶች ግዴታ**</u>

1. የተሟላና ትክክለኛ መረጃ የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው፤
2. እንደአግባብነቱ የቆፈሩትን የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ወይም የሚጠቀሙበትን የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ በአገባቡ የመያዝ ግዴታ አለባቸው፤
3. የፈቃድና የአገልግሎት ክፍያቸውን በወቅቱ የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፤

4. ይህን መመሪያ እና ባለሰልጣኑ የውሃ አጠቃቀምን፣ የውሃ አካላት አጠባበቅን ለመጠበቅ እና የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮን እና አያያዝን አስመልክቶ የሚሰጣቸውን ትዕዛዞች፣ መመሪያዎች የማክበር ግዴታ አለባቸው፤
5. የግንባታና ፍቃድ እና ቁጥጥር ባለሥልጣን በከርሠምድር ውሃ ልማት ሥራ ተያያዥነት ላለው የግንባታ ሥራ እንዲሁም አካባቢያዊ ተፅእኖ ለመጠቀቅ የሚወጣውን መመሪያዎች እና ቅድመ ሁኔታዎች የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፤
6. የመሠረተ ልማት አውታሮች ባለበት የሆኑ ተቋማት በከርሠምድር ውሃ ልማት ሥራ ሂደት ከጉዳት ለመጠበቅ የሚያወጣውን መመሪያዎች እና ቅድመ ሁኔታዎች የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡

33. **<u>መረጃዎችን ስለማሰባሰብ</u>**

ባለስልጣኑ በከተማው ክልል ውስጥ በማንኛውም ሰው ለምተው በሚገኙ የከርሰ ምድር ውሃ መገኛ ቦታዎች ላይ በመገኘት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይችላል፡-

1. ባለስልጣኑ የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ፈቃድ ወይም የከርሰ ምድር ውሃ መጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች  በያዙት ፈቃድ መሰረት ወይም ህጉ በሚያዘው መሰረት ስለሚያካሂዱት ተግባር መረጃ እንዲሰጡት ለመጠየቅ ይችላል፤
2. በባለስልጣኑ አግባብነት ባላቸው ህጎች እንዲሁም በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩት ገደቦችና ሁኔታዎች የተጠበቁ መሆኑን መከታታል፤
3. የውሃ ጥራት ሁኔታዎችን ለመመርመርና ማጥናት፤
4. አስፈላጊ የሆኑ ማንኛውንም መሳሪያዎች ለመትከል ፣ለመጠገን፣ለማንበብ ወይም መፈተሽ፤
5. በውሃ ጉድጓድ ውስጥ ተቆፍረው የወጡትን ነገሮች ለመመርመር፤
6. በማንኛውም ዓይነትና ዘዴ የተወሰደውን ወይም ሊወሰድ ሚችለውን ውሃ መጠን ማረጋገጥ፤
7. የተያዙ እና መያዝ ያለባቸውን መዝገቦች መመርመር፤
8. የማንኛውንም ውሃ ናሙና ወይም የውሃ ጥራትን ሊነካ ይችላል ብሎ የሚገምተውን ማንኛውንም ነገር ለመውሰድ ይችላል፡፡

34. **ስለአገልግሎት ክፍያ**

በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሰጡ ፈቃዶችን ለማግኘትና እነዚህ ፈቃዶች እንዲታደሱ፣ እንዲሰረዙ፣ እንዲለወጡ ወይም እንዲተላለፉ ለሚቀርቡ ማመልከቻዎች ለሚሰጡ አገልግሎቶች አግባብነት ባለው ህግ መሰረት የአገልግሎት ክፍያዎች መከፈል አለባቸው፡፡

35. **ስለ ውሃ ግልጋሎት ዋጋ**

1. በዚህ መመሪያ መሰረት የውሃ ሃብትን ለማንኛውም አገልግሎት ለማዋል የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የውሃ አገልግሎት ክፍያን አግባብ ባለው ህግ መሰረት በዓመት አንድ ግዜ ወይም እንደሁኔታው ባለስልጣኑ በሚያወጣው የግዜ ዘሌዳ መሰረት ክፍያውን መክፈል አለበት፤
2. የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የውሃ አገልግሎት ክፍያን የአገልግሎት መጠየቂያው ውስጥ ከሚጠቀሰው ቀን ጀምሮ በ 30 ቀን ግዜ ውስጥ መክፈል አለበት፤
3. የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የውሃ አገልግሎት ክፍያን ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 በተጠቀሰው ግዜ ውስጥ ካልከፈለ ባለስልጣኑ ባለፈቃዱ ክፍያውን እንዲከፍል የ 30 ቀናት ተጨማሪ የችሮታ ግዜ ይሰጠዋል፤ተጠቃሚው በዚህ የችሮታ ግዜ ውስጥ ክፍያውን ካልፈፀመ የተጠቃሚውን የመጠቀሚያ ፈቃድ በማገድ የውሃ አገልግሎቱን እንዳይጠቀም ያግደዋል፤
4. ማንኛውም የውሃ መጠቀሚያ ባለፈቃድ የውሃ አጠቃቀም ክፍያ ባለመክፈሉ የመጠቀሚያ ፈቃዱ ታግዶ እና ውሃውን እንዳይጠቀም እገዳ ተጥሎበት እያለ የውሃ አገልግሎቱን ሲጠቀም ከተገኘ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይደረጋል፡፡

# **ክፍል ስድስት**

# **ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

36. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በከተማው ክልል ውስጥ ባሉ በተለያዩ ቦታዎች ውስጥ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል በተሰጠ ፈቃድ ወይም ያለፈቃድ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ወይም የውሃ ግንባታ ሥራዎችን ያከናወነ ወይም በማከናወን ላይ ያለ እንዲሁም የከርሰ ምድር ውሃ በመጠቀም ላይ ያለ ማንኛውም ሰው ይህ መመሪያ ከፀናበት ወይም ባለስልጣኑ በብዙሃን መገናኛ ማስታወቂያ ካስነገረበት በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ የከርሰ ምድር ቁፋሮ ሥራውን ለመቀጠል ወይም በውሃው ለመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጠው ለባለስልጣኑ ማመልከት አለበት፤

2. ከላይ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ሳያመለክት የከርሰ ምድር ቁፋሮ ሥራ የሰራ ወይም በመሥራት ላይ ያለ ወይም የውሃ ሃብት በመጠቀም ላይ ያለ ተጠቃሚ በሚቀጥሉት ሰላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ባለስልጣኑ ለመደበኛ ፈቃድ በሚያስከፍለው ክፍያ ላይ ሃምሳ በመቶ መቀጫ ጨምሮ በመክፈል ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፤

3. ሆኖም ተጠቃሚው ከላይ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ካልቀረበ ባለስልጣኑ የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮውን እንዳያከናውን ወይም የውሃ ሃብቱን እንዳይጠቀም ሊያግደው ይችላል፤

4. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ (1) እስከ (3) መሰረት በውሃ ሃብት የመጠቀም ወይም የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ሥራ እንዲከናውን ፈቃድ የሚሰጠው በዚህ መመሪያ መሰረት የተቀመጡት መስፈርቶችን ሲሟሉ ነው፡፡

37. **ስለተጠያቂነት**

ይህን መመሪያ ያላከበረ ወይም አፈጻጸሙን ያሰናከለ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

38. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣኑ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

39. **ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

40. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ዘሪሁን አባተ (ኢ/ር)**
**የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን**
**ዋና ሥራ አስኪያጅ**